# የፅዳት ስራ ድርሻ መጽሔት



**ጁን 2019** | **ቁጥር 1, ቅፅ 1**




## የፅዳት ስራ ላይ ምርምር መስራት ለምን አስፈለገ?

የፅዳት ስራ አስጨናቂ፣ ጉልበት የሚጠይቅ እና ሰራተኞችን ለጉዳት አደጋ ከፍተኛ ስጋት የሚያጋልጥ ነው፡፡ አንዳንድ የፅዳት ሰራተኞች እንዴት ሪፖርት እንደሚደረግ ባለማወቅ እና ስራችን እናጣለን ብለው በመፍራት ያጋጠማቸውን ጉዳት ላያሳውቁ ይችላሉ፡፡



## ምርምሩን የሚሰራው ማን ነው?

የ Washington ግዛት ሕግ አውጪ የደሕንነትና ጤና እመርታ እውቅና መስጠት ፕሮግራም (Safety and Health Assessment and Research for Prevention, SHARP) የፅዳት ሰራተኞች ከፍተኛ ለጉዳት የመጋለጥ ስጋት መጠን እንዲያጠና ጠይቋል፡፡ SHARP የስራ ቦታ ደሕንነትና ጤንነት እንዴት ማሻሻል እንደሚቻል የሚያጠና የ Department of Labor & Industries (ስራና ኢንዱስትሪ ክፍል) ፕሮግራም ነው፡፡

ዓላማው ስለ ስራ ሁኔታና ደሕንነት ችግሮች ከፅዳት ሰራተኞቹ በቀጥታ ለመረዳት ነው፡፡ SHARP የግል ቃለ-መጠይቅ፣ የትኩረት ቡድን ውይይት፣ የስልክ ዳሰሳ ጥናት፣ ግዛት-አቀፍ ዳሰሳ ጥናት እና የስራ ቦታ ላይ የስራ ጫና ግምገማ ያከናውናል፡፡



## የተሳታፊ ምስክርነት

“ወደ ማህበሩ ለመሄድና SHARP ን ለማግኘት የወሰንኩት [ከፍተኛ የስራ ጫናው] ጤናየ ላይ ተፅእኖ ማድረስ በመጀመሩ ነው፡፡ በተጨማሪ በጊዜ ሂደት ስለስራ ባልደርቦቼ ደሕንነት ነው፣ የስራ ጫናው ጤንነታቸው ላይ ተፅእኖ ሊያደርስ ከመሆኑ ባሻገር አንተን እንደ ማሽን የሚያስብህ የስራ ቦታ ላይ መስራት መልካም አይደለም፡፡”

-Ma Cruz de Villar del Amador, 4 አመት የፅዳት ስራ ልምድ

## አብሮ መስራት

በርካታ የፅዳት ስራ ኩፓንያዎች ሰራተኞቻቸው ላየ ስለሚደርሰው ጉዳት ይጨነቃሉ፣ እንዲሁም ጥቂቶቹ ሄደን ሰራተኞቻቸውን እንድንጎበኝ ተስማምተዋል፡፡



ይህ ማለት ስራዎቻቸውን በሚሰሩበት ሰአት መገምገም እና በራ በመስራት የፅዳት ሰራተኞቹ ለሚያጋጥሙዋቸው ችግሮች መፍተሔ ማግኘት እንችላለን፡፡

## ከርስዎ መስማት እንፈልጋለን!

እስከ አሁን የፅዳት ሰራተኞች ያነሰዋቸው የጤናና ደሕንነት ችግሮች የሚከተሉትን እንደሆኑ ገልፀዋል :

- የስራ ጫናና ፍጥነት መጨመር፡፡
- የተሰበረ የፅዳት እቃ፡፡
- የፅዳት ግብኣቶች አቅርቦት እጥረት፡፡
- የደሕንነት ስልጠና አለመኖር፡፡
- ግጭትና ትንኮሳ፡፡
- በመረጃ እጥረትና ፍርሐት ምክንያት ጉዳት ሲደርስ አለማሳወቅ፡፡